# ለሥራ ጤንነትና ደህንነት – በሥራ ጤንነትና ደህንነት ህጎች መሰረት ተግባራት

የሥራ ጤንነትና ደህንነት ህጎች ሞደል ያስፈለገው በሥራ ቦታ ላይ ላሉ ሰዎች ጤንነት፣ ደህንነትና በጎነት ቀጣሪዎች እንክብካቤ እንዲያደርጉ ነው። በዚህ የሚካተት:

- ለጤንነትና ደህንነት ችግር የሌለበት የሥራ አካባቢን ማቅረብና መጠበቅ
- ለሰራተኞች በጎ አድራጎት ሥራቸውን ለሚያካሂዱበት በቂና አመቺ መገልገያዎችን ማቅረብ፣ እና
- ህመምን ወይም ጉዳትን ለመከላከል የሰራተኞችን ጤንነት እና የሥራ ቦታን ሁኔታዎች መቆጣጠር ይሆናል።

## ለሰራተኞች ግዴታ

የርስዎን ሰራተኞች ጤንነትና ደህንነት የማረጋገጥ ግዴታ አለብዎ። ለኮቪድ/COVID-19 ችግር ማስወገድ እንዳለብዎ፣ ወይም ይህ የማይቻል ከሆነ፣ በተቻለ መጠን ችግሩ እንዲቀንስ ማድረግ ይኖርብዎታል።

ሰራተኞች ከኮቪድ/ COVID-19 ችግር መጋለጥ መከላከል፣ ለምሳሌ:

- ከቤት ሆኖ ሥራን ለማካሄድ በማቀናጀት
- ሰራተኞች በአካል የመራርቅን እና ጥሩ ጽዳት ሃይጂን መጠበቅ ተግባራዊ ማድረግ እንዳለባቸው
- ሰራተኞች ካመማቸው ከቤት መቆየት እንደሚያስፈልግ፣ እና
- የሥራ ቦታን በተደጋጋሚና በደንብ በማጽዳት ይሆናል።

## በሥራ ቦታ ላይ ለሌሎች ሰዎች መደረግ ያለበት

በንግድ ሥራዎ ላይ ያለ ሥራ ለሌሎች ሰዎች እንደ ተጠቃሚዎች፣ ደንበኞችና ጎብኝዎች ችግር ላይ ባሉት የጤንነትና ደህንነት ችግር ላይ እንዳልገባ ማረጋገጥ አለብዎት።

ሌሎች ሰዎችን ከኮቪድ/ COVID-19 ችግር መጋለጥ መከላከል፣ ለምሳሌ፣ እነሱ ማድረግ ያለባቸው:

- የአካል እርቀትን ለማካሄድ፣ ይህም ንክኪ በሌለባቸው የእቃ ማድረስና ክፍያዎች
- ጥሩ ጽዳት ሃይጂን ለማካሄድ፣ እና
- ጠቃሚ ካልሆነ በስተቀር ከሥራ ቦታ ላይ እርቆ መቆየት።

## ለሥራ ቦታና መገልገያዎች በሚገባ ለመያዝ ግዴታ

የርስዎን ሥራ ቦታ በደንብ ስለመያዙ ለማረጋገጥ በሥራ አካባቢ ላይ ከኮቪድ/COVID-19 ችግር ጋር ግንኙነት ያደረጉትን ሰራተኞችና ሌሎች ሰዎችን አለማስቀመጥ ነው።

ጤናማ የሆነ የሥራ አካባቢ መፍጠር፣ ይህም ለምሳሌ:

- የሥራ ቦታን በተደጋጋሚና በሚገባ በማጽዳት

- ለአካል መራራቅ እንዲያስችል የሥራ ቦታን አቀማመጥ መቀየር፤ እና
- በሥራ ቦታ ውስጥ የሰዎችን ቁጥር መወሰን ይሆናል።

እንዲሁም በርስዎ የሥራ ቦታ ላይ በቂ የሆነ መገልገያዎችን ማቅረብ እንዳለብዎት፤ በዚህ የሚካተት:

- የእጅ መታጠቢያ መገልገያዎች ከሳሙና፤ ውሃና ከወረቀት ማድረቂያ ፎጣ ጋር
- ሰራተኞች እጃቸውን መታጠብ የማይችሉ ከሆነ፤ የእጃ ማስጃ ሳኒታይዘር፤ እና
- ንጽህና ያላቸውና ለአካል መራራቅ ለሚያስችል የሰራተኛ ክፍሎች።

ሰራተኞች መገልገያዎችን ለመጠቀም በተደጋጋሚ እረፍት ማቅረብ፤ በተለይ እጆቻቸውን እንዲታጠቡ።

## መረጃ፤ ስልጠና፤ መመሪያ እና ቁጥጥር ለማቅረብ ግዴታ

ሰራተኞች በሥራ ቦታ ላይ እራሳቸውን ከኮቪድ/ COVID-19 ችግር ጋር መጋለጥን ለመከላከል ለርስዎ ሰራተኞች ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን ወይም ስልጠና ማቅረብ አለብዎት።

በዚህ ሊካተት የሚችለው:

- እጅን በሚገባ ስለመታጠብ መምሪያ
- ማንኛውም ግላዊ የመከላከያ መሳሪያ እንዴት መግጠምን መጠቀም እንደሚቻል ስልጠና
- እንዴትና መቸ ማጽዳት እንደሚቻል ስልጠና
- ደህንነት ባለው ከቤት ሆኖ ሥራ ለማቀናጀት መመሪያዎች፤ እና
- አደገኛ ከሆነ ከቤት ሆኖ በመሥራት መቆየት መመሪያዎችን መስጠት ይሆናል።

## ለመማከርት ግዴታ

ከኮቪድ/ COVID-19 ጋር በተዛመደ ጤንነትና ደህንነት ጉዳዮች ከሰራተኞች ጋር መመካከር እንዳለብዎትና ታዲያ ሰራተኞች ያላቸውን አመለካከትና አሳሳቢ ጉዳዮች እንዲገልጹ እድሉን መስጠት። የሚያቀርቡትን አመለካከት ግምት ውስጥ ማስገባትና በመማከርት ስለተገኘው ውጤት ሰራተኞችን መምከር።

ከሰራተኞች ጋር የሚማከሩት እርስዎ:

- ስለችግር ግምገማ በሚያደርጉበት ጊዜ
- ችግርን ለመቆጣጠር፤ እንደ ከቤት ሆኖ መሥራት ቅንጂት ወይም በሥራ ቦታ ለአካል መራራቅ እርግጠኛ ለመሆን ለቀረቡት እገዳዎች ስለሚወሰዱ እርምጃዎች ውሳኔ በሚያደርጉበት ጊዜ
- ስለ ሥራ ቦታ መገልገያዎች ውሳኔ ሲያደጉ፤ እና
- በሰራተኞች ጤንነትና ደህንነት ላይ ችግር ሊፈጥር ስለሚችል ሌሎች ለውጦችን በሚታቀድበት ጊዜ ይሆናል።

ለማንኛውም የተስማሙበት መማክርት ሂደት ላይ መከታተል አልብዎት። የጤና እና ደህንነት ተወካዮች ካሉ፤ በመማክርቱ ላይ እንዲካተቱ ማድረግ አለብዎት።

## ለበለጠ መረጃ

ስለኮቪድ/COVID-19 እና ለሥራ ጤንነትና ደህንነት የበለጠ መረጃ ለማግኘት በድረገጽ፡ Safe Work Australia website ላይ ገብቶ ማየት።